# ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ
# Coalition for Unity and Democracy Party (Kinijit)

e-mail kil@kinijitinternational.org


**Date: October 15, 2006**
**KIL_PR__AMH 008**

## ግለሰባዊ አመባገነንነትና ፈላጭ ቆራጭነት በቅንጅት ውስጥ ቦታ የላቸዉም!
## ከቅንጅት አለም አቀፍ የፖለቲካ አመራር የተሰጠ መግለጫ፣

«ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ የሰሜን አሜሪካ ተጠሪ ጽ/ቤት» በሚባል ድርጅት ስም በሻለቃ ዮሴፍ ያዘው «በሰሜን አሜሪካ ቅንጀት ውስጥ ቅንጅት ኢንተርናሽናል አመራር በፈጠረው ችግር የተወሰደ ውሳኔ» በሚል በተበተነ ጽሁፍ መነሻነት የቅንጅት አለም አቀፍ የፖለቲካ አመራር አስቸኩዋይ ስብሰባ አካሂዶ የሚከተሉትን ነጥቦች ለህዝብ ግልጽ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል፡-

- ከሁሉ አስቀድሞ ይህ መግለጫ በተሰጠበት ወቅት ያስከተለው ወዥንብር ለነጻነት ለዴሞክራሲና ለአንድነት በጋራ በቆመው ወገናችን ላይ የሚያሳድረውን ብስጭት እና ከሁላችን በፊት መረጃው በተሰጠው የወያኔ ድረገጽ አማካይነት በወያኔ ቤት የፈጠረውን ፈንጠዝያ ስናስብ ሃዘናችን የበረታ ሆኗል፡፡

- ሻለቃ ዬሴፍ የአለም ዓቀፍ አመራሩ አባላት ከሰጧቻው የውክልና የስራ መደብ ስልጣን እና ገደብ በመውጣት በመግለጫው ላይ ያሰፈሯቸውን፣ የአለምአቀፉን አመራር እንቅስቃሴ ለመግታትም ሆነ በአመራሩ ውስጥ የሚገኙ ․ አባላትን ለማገድ የሰጡት መግለጫ ህገወጥ መሆኑን

- በመግለጫው ውስጥ አለምአቀፍ አመራሩን በሚመለከትም ሆነ በውስጡ በሚገኙ አባላት ላይ ምንም አይነት እርምጃ መውሰድ የሚያስችል ስልጣን እንደሌላቸዉና ድርጊቱ በአምባገነንነትና በማን አለብኝነት የተፈጸመ መሆኑን

- አንዲህ አይነቱን ሃላፊነት የጎደለው መግለጫ ከማውጣታቸው በፊት የቤተሰብ ችግር አለብኝ በሚል ምክንያት በተከታታይ የአመራሩ ስብሰባዎች ላይ መገኘት ማቆማቸውን፣ በተለይ ደግሞ አለምአቀፍ አመራሩ ከቅንጅት ኢትዮጵያ የተሰጠውን ሃላፊነት በአግባቡ እየተወጣ አለመሆኑን በመሪዎቻችን እና በቅንጅት ደጋፊዎች የሚቀርብብን ሂስ መሰረት ያደረገ የራሳችንን የግምገማ ስራ ለማከናወን በሚጠሩ ስብሰባዎች ላይ ባለመገኘት

- ተጠያቂነት የጎደለዉ በውል መድረሻው ምን እንደሆነ የማይታወቅ አንቅስቃሴ በግል መጀመራቸው ያስገረመንና ያሳዘነን መሆኑን ስንገልጽ ልባችንን ሃዘን ተጭኖት ነው፡፡

ሻለቃ ዮሴፍ በሃገር ቤት በስቃይ ውስጥ ባሉ የቅንጀት መሪዎችና በአለም አቀፍ አመራሩ ውስጥ በምንገኝ የአመራሩ አባላት የተሰጣቸውን ሃላፊነት እና አደራ፣ ለቅንጅት አለምአቀፍ አመራር አንዲመለስ በተወሰነውና ለአንዲህ አይነቱ ደርጊት መፈጸሚያ ለማድረግ ለአመራሩ አንዳይመለስ በተደረገው የቅንጀት ድረ ገጽ የፈጸሙት ህገወጥ ድርጊት ቅንጅቱን እና ትግሉን የሚጎዳ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ድርጊቱ አሳሳቢ በመሆኑም

1. ከኦክቶብር 15 ቀን 2006 የቅንጀት አለምአቀፍ አመራር ሁኔታውን ለመመርመር በጠራው አስቸኳይ ስብሰባ በተገኙት ስምንት የአመራር አባላት ከእዚሁ እለት ጀምሮ ሻለቃ ዮሴፍ ያዘው ቅንጀትን በመወከል በየትኛውም የሃላፊነት ቦታ አንዳይሰሩ በጊዚያዊነት ያገዳቸው መሆኑንና ይህንንም ህገወጥ ድርጊት አጣርቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን ይገልጻል፡፡

2. ግለሰባዊ አመባገነንነትና ፈላጭ ቆራጭነት በቅንጅት ውስጥ ቦታ የሌላቸዉ በመሆኑና ከዚህ አንጻር የተፈጸመው ጥፋት ከፍተኛነት ቢያሳስበንም ሁላችንም ሁኔታውን በርጋታና በጥሞና እንድናጤን እንደዚሁም ከቅንጅት መርሆዎች ውጪ የሚደረግ ማንኛዉንም ይህን መሰል እንቅስቃሴን ነቅተን እንድንጠብቅና አንድነታችንን እነድናቆይ እያሳሰበ የቅንጀት አለምአቀፍ አመራር ወደፊት የሚሰጣቸውን ውሳኔዎቸና መመሪያዎች በትእግስት አንዲጠብቁ ለቅንጅት አባለት እና ደጋፊዎች ጥሪያችንን አንቀርባለን፡፡

የቅንጅት አለም ዓቀፍ አመራር
ኦክቶብር 15 ቀን 2006
ዋሽንግተን ዲሲ